# ሹገር ዳዲና ዘመናዊው ጠለፋ

ከበልጅግ አሊ

የሴቶች ጥያቄ በሚነሳበት ግዜና ብዙው የዘንድሮ ፓለቲከኛ ከንፈሩን ከመምጠጥ ከማዘን አልፎ ለሴቶች ተሳትፎ የረባ ነገር በማያደርግበት ወቅት ፖለቲካው የወንዶች እድር ነው ቢባል ምንም የሚደንቅ አይሆንም።ብዙም ፖለቲከኛ የሴቶች ቀን በመጋቢት 8(March 8) ብቻ ሊታወስ የሚገባው እንጂ የቀን ተቀን ትግል የሚያስፈልገው አይመስላቸውም።እንዲያውም ተደራጅተው የሚታገሉትን ሴቶች በሞራልና በማቴሪያል ከመርዳት ይልቅ ሌላ አቃቂር ሲያወጡ ነው የሚታዩት።በተለይ አንዳንዱ የዘመኑ አደርባይ ፖለቲከኛ ከረባቱን አንገቱ ላይ አድርጎ በየስብሰባው ሲያንዛርጥ የሚውለውና ሲቀናው ደግሞ አዲስ አበባ እየሄደ እሸሼ ገዳሜውን የሚረግጠው በሃገር ቤት በእህቶቻችን ላይ የሚሰራውን አስከፊ ተግባር ስናየውና ስንሰማው ስብዕናችንን የሚያስጠላን ሆኖ እናገኘዋለን።

በተወሰነ የሀገራችን ታሪክ ውስጥ ሴቶች ያበረከቱት ታላላቅ ገድል ተፅፎም አያልቅ። በየቤቱ ተደብቆ የቀረውን የእህቶቻችንን ታላቅ አስተዋፆዋቸውን ደግሞ ቤቱ ይቁጠረው እንጂ ትምክተኛ ወንዶች አውጥተን ባለቤቱ እንዲህ መክራኝ ነው ፣ እህቴ እንዲህ ያለ ሃሳብ አምጥታ ነው ለዚህ ታላቅ ስራ የበቃሁት ብለን አደባባይ ላይ የሴቶችን ብልህነት ከማውራት ይልቅ የራሳችን ጅግንነትና የፈጠራ ችሎታ አድርገን ማቅረብን እንወዳለን።

ፓለቲካው ከወንዶች እድርነት አልፎ የእህቶቻችን ተሳትፎ ሲጨምር ብቻ ነው ለድል የምንበቃው ዴሞክራሲም የሚሰፍረው  ብዬ ግልፅ አድርጌ ብናገር አፉን የሚያጣምምና የሚያሽሟጥጥ ፖለቲከኛ ብዛቱን ለመገመት ብዙም አያዳግትም። የሆኖ ሆኖ ግን እኔ በበኩሌ ካለኝ ልምድ አንባቢያንን ማካፈል ቢያስፈልግ በቀይ ሽብር ወቅት በትግል ውስጥ በቆራጥነት ሲታገሉ ስንት ጀግኖች እህቶቻችን እጥፍ የሆነ ግርፋትና ስቃይ ከወንዶች ጓዶቻችው በላይ እንደደረሰባቸው ምስክርነቴን ልሰጥ እችላለሁ። በዛ ዘመን

እኔስ እሰዋለሁ በእንባሽ በኩሬው ላይ
ስትሸማቀቂ ሲከፋሽ እንዳላይ

ብለን ከእህቶቻችን ጋር በክብር በቀይ ሽብር ዘመን ተከባብርን ፣ ተፋቅረን ለአንድ አላማ የቆስልን ፣ አካላችን የጎደለ ብዙ ነን።በዚያም አሰቃቂ ዘመን ሀገራችንን ከታላቅ ቦታ ለማድረስ በሚደረገው ጥረት ህይወታቸውን የገበሩ እህቶቻችንን ታሪክ በክብር ቦታ በማይፋቅ ቀለም ፅፎ አስቀምጧቸዋል። እነዚህ እህቶቻችንን ደግሞ ከወንዶች በተለየ በብልታቸው ብረት እየተጨመረ ፣ ክብራቸውን እየተደፈረ፣ ስንት አይነት ስቃይ ውስጥ እንደነበሩ የምናስታውስ ብዙ ነን።

ለምስክርነት ያህል አንድ በቀይ ሽብር የተመታች ጓዳችን ለሞት ከእንቅልፏ ተቀስቅሳ ስትነሳ የእያንዳንዳችንን ስም እየጠራች ትግሉን እንድንቀጥል ከተነናገረች በኃላ የትግሉ ነው ሕይወቴን እየዘመረች ወደ ሞት ስታመራ ሁላችንም እሷ የሰጠችንን አላፊነት እንዴት ነው የምናስፈፅመው ብለን ስንባዝን ኖረናል። እኔ እስከዛሬ የዛች ጓዳችን  ድምፅ ይሰማኛል አሁንም ቢሆን ያ  ድምፅ  እየመጣ እንደሚረብሸኝ ነው።ስንቶቻችን ነን ታዲያ የእነዚህን እህቶቻችንን አላማ ከግብ ለማደረስ በቆራጥነት ትግሉን መቀጠል የቻልነው? ስንቶቻችንስ ነን በዘመኑ የሰለጠነ ፖለቲካ በውጭ አገር የሰበሰብነውን ነዋይ በመጠቀም እህቶቻችን ላይ ክብረ ነክ ተግባር የምንፈፅመው?

ለነገሩ የሴቶችን ጥያቄ ሳነሳ የጓዴን ትዝታ ሳላነሳው እንዳላልፍ አመጣሁት እንጂ ዛሬ ለአነሳው የፈለግሁት አርዕስት የዘመኑን የሰለጠነ የጠለፋ ተግባርን ለአንባቢያን  ለማቅረብ ነው።

ጥንት ድሮ ሰው ዘሩ ተቆጥሮ በሚያገባበት ዘመን ትዳር መመስረት አቅም ከሚፈቅደው ጋር ብቻ ነበር። በተለይ ሴቶች የመምረጥ መብት ያልነበራቸው ግዜ ቤተሰቦች ለነእርሱ ቆመው ነበር የትዳር አጋሮቻቸውን የሚመርጡላቸው። ወደዱም ጠሉም ቤተሰብ ከመረጠላቸው የትዳር ጓደኛ ጋር አብሮ ለመኖር ይገደዳሉ። ይህ  ጥንት የሚባል ግዜ ሳይሆን እኛ በደረስንበት ግዜም ይደረግ እንደነበር አስታውሳለሁ።አሁንም ቢሆን በየገጠሩ ይፈፀማል። ታዲያ እንቢ ያለ ቤተሰብን ጉልበተኛ ልጁን በመጥለፍ ይወስድ እንደነበር የታወቀ ነው። በከተማ ውስጥ እንኳ በቅርብ ግዜ የደርግ ካድሬዎች ይህንን እንደሚያደርጉ አስታውሳለሁ።መንግስት በሰጣቸው መብት በመጠቀም የደርግ ካድሬዎች ስንቱን ቆነጃጅት እያሰፈራሩ የግል ስሜታቸውን ማርኪያ አድርገው እንደነበረ አስታውሳለሁ። እንቢ ማለት ቤተሰቧን ችግር ውስጥ መክተት ስለሆነ እሽ ብላ ለሱ ተገዢ ሆና መኖር ትገደድ ነበር።

እኔ እንኳን በቅርብ የማስታውሰው አንድ አንዳርጌ የሚሉት ካድሬ አንዲት ልጅ ጠልፎ ስፈራችን ይዞ መጥቶ ጓደኞቹ ተሰብስበው ሲጠጡ ሽንት ቤት ልሂድ ብላ የተሰጣ ነጠላ አደርጋ በመጥፋትዋ ምክንያት ሰፈሩም ጉድ ሲል የሰፈሩ ልጆች በዘመኑ የገጠሙት

ለማግባት ያሰፈሰፈ
አንዳርጌ ሴራው ከሸፈ።
የሚለው ግጥም ትዝ ይለኛል።

ከዛም በዛች በልጅት ላይም ሆነ በቤተሰቦቿ ላይ የደረሰውን መገመት አያቅትም ህግ ወጥቶለት የኢሰፓን አባል የሰደበ ፣ ለመስደብ ያሰበ ፣ ወይም ያዋረደ በህግ ይቀጣል የሚል ህግ በተደነገገበት አገር የተከበረው የኢሰፓውን አባል የትዳር ጥያቄ እንቢ ያለች ሴት ምን እንደሚከተላት በህግ ባይፃፍም ክብረ ነክ ነውና ጠንከር ያለ ቅጣት እንደሚጠብቃት ምንም ጥርጥር የለውም።

በሌላ ወቅት ደግሞ በኢሊባቡር ክፍለ ሃገር የኢሰፓአኮ የቁጥጥር ኮሚቴ አላፊ የነበረው ግለሰብ እራሱ ላወጣው መጠይቅ (ክራይቴሪያ) የምታሟላው ልጅ ሰትፈለግ ተከርሞ ነበር። „ካድሬው መጠይቃቸውን  የምታሟላ እየፈለጉ ነው“ የሚለው የአደባባይ ሚስጥር ሆኖ ሳለ በድንገት አንዲት  ለጋ ወጣት ላይ አበሳው ደረሰ። ይህቺ ነች መጠይቁን የምታሟላው ብሎ ካድሬው ስላለ የጎሬ ከተማ ሲታመስ ነበር ። ይህቺ ጉብል አንድ ሚስኪን የግብርና ሰራተኛ ጓደኛ ነበራት።በዚህም ምክንያት ጠቅላላው የአውራጃው የግብርና ሰራተኛ በጠላትነት ተፈርጆ ሲረገድ እንደነበር የማስታውሰው ነው። ያም የፈረደበት ልጅ ከአውራጃው ተቀይሮ ወደ አንድ እሩቅ የነበረ ወረዳ የተመደበ ሲሆን ወደ ጎሬ ለጉዳይ በመጣ ጊዜ ባስቸኳይ ከከተማው  እንዲወጣ ሁላችንም ስንመክረው ነበር።የሁለቱ ተመጣጣኝ እድሜ ያላቸው ወጣቶች ፍቅር ግዜ በሰጠው ካድሬ ተሰናክሎ መቅረቱ ለምን ግዜውም ቢሆን በአካባቢው ነዋሪዎች የማይዘነጉት ነው።

ግዜው እረጅም ቢሆንም በከፋ ክፍለ ሃገር ፣ በከፋ አውራጃ ፣ በቦንጋ ከተማ የተደረገ ጠለፋንም ተከታትዬ ነበር።። ሁኔታው ጠላፊውና ተጠላፊዋ የተስማሙበት ቢሆንም አባት ልጄን ለመጤ(በአካባቢው ያልተወለደ ማለት ነው በተለይ የመንግስት ሰራተኛን ይመለከታል) ብለው ስላስቸገሩና ልጅም በመሃል ስላረገዘች በአስቸኳይ የተገኘው መፍትሄ መጥለፍ ነበር።ጠላፊዎች በመኪና ተጭነው ከልጅቷ ጋር በተስማሙበት ግዜ በድብቅ ቦታ ዝግጅታቸውን ጨርሰው  ጓደኛሞች ተሰብስበው ወደ ቦንጋ ከተማ ወጡ። ለትብብር ያህል የአውራ ጎዳና ሰራተኞችና የግብርና ሰራተኞች እንዲረዱ ተጠይቀው ለድፍረቱ ትንሽ ተቀማምሶ ወደ ቦንጋ ከተማ ትምህርት ቤት ተወጣ።

ተማሪዎቹ ሲለቀቁ ከመኪናቸው የሚጠልፈው ግለሰብ ወጥቶ በርበሬ ከኪሱ አውጥቶ ተማሪዎቹ ላይ ከበተነ በኋላ ተጠላፊዋ ጎትቶ እመኪና ውስጥ ከቶ ተነስተው ከቦንጋ ከተማ ወጥተው  ዝግጅት ተደግሶ በሚጠበቅበት ቦታ ይዘዋት መጡ። ቦንጋ ከተማ በጠለፋው ወሬ ተጥለቀለቀች፣ በርበሬ አይኗ ላይ ጨመረ የሚለውም ተወራ።ለነገሩ በርበሬው ወደ ሌሎቹ ነው የተበተነው ለዛውም በጣም ጥቂት የሆነ ምጠን ነበር። አባት ተናደው ላንድ ሮቨር መኪናቸውን አስነስተው ፍለጋ ተነሱ። ጎረቤት ተከተለ። ግማሹ ደግ አደርገ ብሎ ሲያወራ ፣ ሌላው ደግሞ አባቷ ይገሉታል ይላል።

ጠላፊዎች ታዲያ ከቦንጋ ከተማ ወጥተው ወደ ጅማ ያለውን መንገድ ጀመሩ። አባትየው ደንፍተው እየበረሩ ሲወጡ የአውራ ጎዳና ሰራተኞች እንደተመከሩት መንገዱ ላይ ኮረኮንች ሞልተው ሲያስተካክሉ ደረሱ አባትየው ተንኮል ስላልመሰላቸው ሰራተኞችን እንዲፈጥኑ ይለምኑ ገቡ።

ጠላፊዎቹ ትንሽ እንደራቁ መንገዱ ተጠርጎላቸው አለፉ ከቦንጋ ከተማ ሲወጡ ወደ ሚዛን ተፈሪና ወደ ጂማ የሚወስደው መገንጠያ ላይ የግብርና ሰራተኞች መኪናቸውን ተበላሽቶ መሃል መንገድ ላይ ቆመው ሲሰሩ ደረሱባቸው ። አባትየው ከመኪና ወርደው ጠላፊዎቹ ወዴት እንደሄዱ ቢጠይቁ የግብርና ሰራተኞቹ የጠላፊዎቹ ጓደኞች ሰለነበሩ ወደ ተሳሳተው ወደ ሚዛን መንገድ እንደሄዱ ነገሯቸው። አባትየው ቀድመውም ስለጠረጠሩ ጠላፊው ይኖርበት ወደ ነበር ወደዛው አመሩ። እዚም ሲደርሱ ማንም ሊያገኙ አልቻሉም። ደንፍተው ጮኸው ወደ ቤታችው ተመለሱ።

ከዛም የሰፈር ሽምግሌ ተሰብስቦ ይቅርታ ተጠይቆ አባታየውም የልጃቸውን ማርገዝ ሰምተው ይቅርታ አድርገው እስከ አሁን ድርስ ተጋብተው በደስታ የአራት ልጆች አባትና እናት ናቸው። ይህ ታሪክ በተሳካውና በፍላጎት የተደረገ የጠለፋ ስነስርአት ቢሆን ተጠላፊዋም ምን ያህል እንደተጨነቀችና እንዳለቀሰች የማስታውሰው ነው።እኔን ትዝ የሚለኝ አባትየው ተደፈርኩ ብለው በንዴት እንዴት ስውነታቸው ይንቀጠቀጥ እንደነበር ነው።በኋላ ግን ታዲያ  ልጁን ወድደውት ታሪኩን እራሳቸው ለሌላው

ሲተርኩ ሰምቻለሁ።አይ እነ በልጅግ ቀድማችሁ ይህንን ብትነግሩኝ ኖሮ ያን ሁሉ አሳፋሪ ተግባር አልፈፅምም ነበር ብለውም በኛ አሳበውም ያውቃሉ።

በፍቅርና በመግባባት ከተደረገው ውጭ ልጅቷም ሳትፈልግ ተገድዳ ከተጠለፈች በኋላ እቤት ውስጥ ተዘግቶባት ልጅ ደጋግማ እስከምትወልድ ድረስና ሕይወቷን በሞላ ለልጆቿ እስከምትሰጥ ድረስ እንደተዘጋች ትኖር እንደነበር የሚታወስ ነው። ስንት ሴቶች እህቶቻችን በእንደዚህ አይነት እስከአሁን እንደሚሰቃዩ ለመገመት አያዳግትም። ታዲያ ይህ ሁኔታ አሁን በሰለጠነው ሁኔታ ተቀየረ እንጂ አልቀረም።

ለምሳሌ የዘመኑ ጠለፋ አገር ውስጥ የሚደረገው ብቻ ሳይሆን በውጭ ሃገር እየተደረገ ያለውን በፅሞና መመልከት ያሻል። አንድ ጎረቤታችሁ የምታውቁት በእድሜው የገፋ ወንደላጤ ሰው ትዳር ልይዝ ሃገሬ ሊሔድ ነው ቢላችሁ ደስ እንደሚላችሁ አልጠራጠርም።ግለሰቡ እድሜው የገፋ ስለሆነ ትዳር ያስፈለገዋል ብላችሁ ስለምታምኑ ለቅርብ ታቦት ትዳር ስጠው ብላችሁ ስትሳሉ ከነበረም ስለታችሁ ስለሞላ ምስጋና ልታቀርቡ ትችላላችሁ። የሆነ ሆኖ ግን ከሃገር ሲመለስ ማግባቱን ከነገራችሁ በኋላ ባለቤቴ ብሎ አንዲት ኩፍኝ ያልወጣላት ዕፃን ልጅ ፎቶ ቢሳያችሁ ችግሩን በስለት ያመጣችሁት እራሳችን ነን ብላችሁ እራሳችሁን ወቅሳችሁ ታውቃላችሁ?ወይም ደግሞ ጎረቤታችሁ የሆነ ሰው የልጆቹን እናት ፈትቶ ሀገር ቤት ተመልሶ ገና ድብብቆሽ ተጫውታ ያልጠገበች የልጁ ልጅ የምትሆን አግብቶስ ቢመጣስ? ይህና ይህንን የመሳሰሉት የተለመደ ተግባር ሆኑዋል።

ትዳር ጥሩ ነው ። በተለይም ከሃገር ልጅ ጋር ትዳር ጥሩ ነው። የሚከፋው ግን በውጭ ሃገር የተገኘውን ነዋይ ተመክቶ ህፃናት ልጆችን አግብቶ መጥቶ በአንድ ቤት ውስጥ ቆልፎ ልጅ እስከምትወልድ ከሰው አላገናኝም ብሎ ቋንቋ ሳያስተምር ከማንም ሳያገናኝ የቴሌፎን ካርድ ገዝቶ እየሰጠ፣ሰው ሲናፍቅሽ እናትሽ ጋር ደውይ እያለ እህቶቻችንን የሚያሰቃይ ቁጥሩ እየጨመረ ነው። ይህ ሁኔታ እየበዛ የመጣ መሆኑን የምታውቁት ሚስትና ባል እናገናኛለን የሚሉ ደላላዎች በዚሁ በምዕራብ ሃገሮች እየበዙ መምጣታቸው የሚታወቅ ነው።

ይህንን የመሳሰለውን የዘንድሮ የሹገር ዳዲዎች የዘመናዊ ጠለፋ ስነስርአት ብዙዎቻችን እንደማንዋጋውና በግለሰብ ከአዛውንቱ ጠላፊ ጋር መጣላት እንደማንፈልግ የታወቀ ነው። በተለይ አዛውንቱ ከረባቱን አንጠልጥሎ በየስብሰባው የሚያንዛርጥ ከሆነ ደግሞ በዚህስ ቢወነጀል ማን ሊሰማ። በፖለቲካው ክፍፍል የደረሰብኝ ስም ማጥፋት ነው ብሎ ደጋፊዎችን ያሰልፋል እንጂ ትምክተኛው በቀላሉ እጁን አይሰጥም። ታዲያ በውጭ አገር የተቸገረች ጉብል ወደ ሴቶቹ ፈረንጆች ጋር መሮጥ እንጂ እኛማ እኛ ነን።መብቷን ለማስከበር ብዙዎቻችን ምንም ጥረት አናደርግም።እንዲያውም ከአገር ቤት ችግር ያወጣትን እከሌን የፈነገለች ነች በማለት ከህብረተሰቡ ለመነጠል የሚደረገው ጥረት ብዙ ነው። ከአገር ቤት ሰላአመጣት የእርሱ ባሪያ ተገዢ ሆና መኖር እንዳለባት ሽንጣቸውን ይዘው የሚከራከሩ ብዙ ናቸው። አንዳንዱማ ይባስ ብሎ ተታለልኩ በማለት ጨርቄን ጥዬ ልሂድ ብሎ ሲቀባዥር ነው የምናየው።

በሌላው በኩል ደግሞ ወደ ሃገር ቤት ተመልሶ ሄዶ በወግ በማዕረግ በአዲሱ አባባል „ጥፍር አስነቅሎ“ ትዳር ይዞ በቅርብ እወስድሻለሁ በማለት ቃል ይገባና አልተሳካም በሚል ምክንያት እራሱ እየተመላለሰ ልጅ አስወልዶ ከዛው ከሃገር ቤት ቀብድ ለመያዝ የሚጥር አለ።ሁለት ሶስት ካልደጋገምሽ አልወስድሽም እያለ ሚስቱን ሃገር ቤት ያስቀመጠ እንዳለም የምናውቀው ነው። ከቤት እንዳትወጣ ለቁጥጥሩ እንዲያመቸው ወስዶ እናቱ ቤት ያስቀምጣትና በሚስትና በአማት ግኑኝነት ምክንያት ስትቃጠል የምትኖር ስንት እንደለች ቤቱ ይቁጠረው።

የሴቶች እህቶቻችን ችግር ደግሞ በየአረብ ሃገሩ እየተሰደዱ በየባለጌው አረብ የሚደርስባቸውን ስቃይ ብዙ ነው። ይህንን ስቃይ ሁላችንም በንዴት የምንናገረው ሲሆን የወያኔ መንግስት አቀንቃኞች ግን በዚህ የሰውን ልጅ የመሸጥ የመለወጥ ተግባር ከላይ እስከ ታች ተነክረውበት ዛሬ በሃገራችን ገና የእናታቸውን የጡት ወተት ከንፈራቸው ላይ ያልደረቀ ዕፃናት ሳይቀሩ ወደ አረብ ሃገር ሲያግዙ ምንኛ ጭከና እንደሆነ ለመግለፅ ቃላት ያጥረኛል። በእነዚህ አረብ ሀገር ያለውን ኑሮ ኩለው አሳምረው የሚደልሉ የወያኔ አጫፋሪዎች ያለውን ሁኔታ እንደ ንግድ እንጂ እንደ ወንጀል ወያኔም ሆነ አቀንቃኞቹ አስበውት አያውቁም።

የሃገራችን ሁኔታ በህብረተሰባችን ላይ ታላቅ ችግር ውስጥ ከቶናል። ህዝቡ በችግር ምክንያት ክብሩና ኩራቱን እንዲጥል በወያኔና በአቀንቃኞቹ ጥረት እየተደረገ ነው። ከውጭ እየመጡ ከላይ የጠቀስኩትንና ሌሎችንም ግፎች የሚፈጽሙትን በውጭ ያሉትን ተቃዋሚዎች ያዳክሙልኛል በማለት

ወያኔ በሩን ከፍቶ እያስተናገዳቸው ነው። በሃገራችን ውስጥ በአሁኑ ግዜ ወጣቱን ለአደገኛ ዕፅ የሚዳርጉት ሁሉ ከዚሁ ከውጭ የሚሄዱት ናቸው። ብዙ ብዙ እኔ ያልጠቀስኩት ጉዳዩች አሉ። ይህንን ሁሉ ታዲየ የሚፈታው ቢኖር ትግሉን በማጠናከር የወያኔን መንግስት ማስወገድ ብቻ ነው ቀዳሚ ቦታውን መያዝ ያለበት። አልያ ግን ሁኔታው እየሰፋ ሄዶ ማስተካከል የማይደረስበት ደረጃ እንደርሳለን።

በውጭ የሚገኘው ፖለቲከኞች የሴቶች ጥያቄን ለአለም አቀፍ የሴቶች ማህበር አባላት ተታግለው ነፃ ይውጡት በሚል ሁኔታ ነው መሰል ብዙም መግለጫ አላይም።ይህ ደግሞ ትክክል እንዳልሆነ ልንረዳው ይገባል። ከዚህ አይነት ተግባር ያልፀዱ ግለሰቦች በፖለቲካ መሪነት ከሚቀመጡ እራሳቸው ግለ ሂስ እያኪያሄዱ ወይ ሁኔታውን ቢያስተካክሉ ወይም ደግሞ አንድ ሰው ነጻ ማውጣት ካልቻሉ የኢትዮጳያን ህዝብ ነፃ ማውጣት አይችሉምና ከትግሉ ሜዳ እራቅ ሊሉ ይገባል እላለሁ።

ስለእህቶቻችን የሚስብ ሁሉ በሰላም ይክረም !!!!

በልጅግ አሊ
የካቲት 2000